SMITTSKYDDSBLAD

Patientinformation frånSveriges smittskyddsläkare

Amarinja – Latent tuberkulosinfektion – när behandling ges

# ድብቅ ሳንባ ነቀርሳ ኢንፈክሽን - ህክምና በሚሰጥበት ወቅት

የታካሚው መረጃ ከስዊድን ተላላፊ በሽታ ሐኪም

## ይህንን መረጃ ለምን አገኘሁት?

አንድ ምርመራ ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን እንዳለቦት አሳይቷል። ዶክተርዎ በኋላ ላይ በሳንባ ነቀርሳ የመታመም ያልዎትን አደጋ ለመቀነስ፥ ህክምና እንደሚያስፈልግዎ ገምግሟል።

እዚህ ምን ማሰብ እንዳለብዎት ይማራሉ።

## ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ምንድን ነው?

ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ማለት፥ በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ተይዘዋል ማለት ነው፣ ነገር ግን በእሱ አልታመሙም ማለት ነው። አንድ ሰው በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ሲጠቃ፥ የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርዓቱ ምላሽ ይሰጣል፤ ይህም በደም ምርመራዎች ወይም በቆዳ ምርመራዎች ሊለካ ይችላል። በበሽታው የተያዙ አብዛኛዎቹ ሰዎች፥ ጤናማ ሆነው ይቀጥላሉ። ነገር ግን በኋለኛው ህይወታቸው፡ በሳንባ ነቀርሳ የመታመም አንነስተኛ አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል።

በቅርቡ በበሽታው ለተያዙ ሰዎች፣ ለነፍሰ ጡር ሴቶች፣ በቅርቡ ለተወለዱ ህጻኖች፣ ለልጆች፣ ለታዳጊዎች እና በህመም ወይም በመድኃኒት ህክምና ምክንያት፥ የተዳከመ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ላላቸው ሰዎች፥ በኋላ ላይ የመታመም አደጋው ከፍተኛ ነው።

## ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ያስተላልፋል?

አይ፣ ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ተላላፊ አይደለም። የቲዩበርክሎሲስ በሽታ የሚተላለፈው አንድ ሰው ሲታመም እና የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በሳንባ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው።

## እኔ ለድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ሕክምና ማድረግ ያስፈልገኛል?

አዎ፣ ዶክተርዎ በኋላ ላይ በሳንባ ነቀርሳ የመታመምዎን አደጋ ለመቀነስ፥ ህክምና እንደሚያስፈልግዎ ይገመግማል።

## ስለ ምን ማሰብ አለብኝ?

ከህክምና በኋላ፡ ሁሉም ባክቴሪያዎች እንደጠፉ ለመለካት የሚያስችል ምንም መንገድ የለም እና ወደፊት እንደገና በበሽታው ሊበከሉ ይችላሉ።

ምናልባት ወደፊት ረዘም ላለ ግዜ የሚቆይ (ሶስት ሳምንታት በላይ) የማሳል ሁኔታ፣ በሌሊት በላብ የመዘፈቅ ችግር፣ ትኩሳት ወይም ያልታለመደ የክብደት መቀነስ ካጋጠምዎት፥ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ እንዲደረግልዎት ሃኪምዎን መጠየቅ ይኖርብዎታል፡ ቀደም ሲል ለተደበቀ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ሕክምና ማግኘትዎን ይግለጹ።

## የግንኙነት መረጃዎች (Kontaktuppgifter)

የታካሚዎች መቀበያ ክሊኒክ (Mottagning)…...……………………………………………...

……………………………………………………………………...……………………

ስልክ ቁጥር (Telefon)………………………………………………………………………